# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል
## 20 ኛ ሳምንት
## አስቴር - ክፍል አንድ

**ዓላማ**
- ስለ ጾምና ጸሎት ኃይል እና እግዚአብሔር ለሁሉም ዓለማ እንዳለው መማር

**የሚጠና ጥቅስ**
- ***"አስቴርም በሚያዩአት ሁሉ ዓይን ሞገስ አግኝታ ነበር።"*** አስቴር 2÷15

**ምንባብ**
- ዛሬ አስቴር ስለተባለችው ወጣት ሴት ታሪክ ክፍል አንድ እንማራለን።
- በዚህ ትምህርታችንም እንዴት ንግሥት እንደሆነች እናጠናለን።
- ንጉሥ አርጤክስስ፣ አስቴር እና መርዶክዮስ የሚሉትን ስሞች እያስታወሳችሁ እንዴት ንግሥት እንዳሆነች እናጠናለን።
- በእግዚአብሔር ፈቃድ በሚቀጥለው ትምህርታችንም በአስቴር አማካይነት እግዚአብሔር  እንዴት ሕዝቡን እንደታደገ እንማረለን።

**ትምህርት**
- *'አርጤክስስ'* የተባለው የፋርስ ንጉሥ ነበር። 'አስጢን' የተባለች ቆንጆ ሚስት ነበረችው።
- ንጉሡ ለመንግሥቱ አገልጋዮችና ባለሞሎች ታላቅ ግብዣ አደረገ። በግብዣውም ብዙ ምግብና መጠጥ ከወርቅ በተሰራ ሳህንና ኩባያ ይቀረብ ነበር።
- በግብዣው ሰው ሁሉ ከተደሠተ በኋላም ንግሥቲቱ 'አስጢን' የንግሥና ዘውድ ደፍታና በከበሩ ጌጣጦች አሸብርቃ እንድትመጣ ንጉሱ አገልጋዮቹን ላከባት። 'አስጢን' ግን እንቢ አለች።
- 'አርጤክስስም' ንግሥትነትዋ እንዲቀርና ሌላ በእርስዋ ምትክ ንግሥት እንድታዘጋጅ ወስኖ ÷አዘዘ።
- ለንግሥትነት የምትሆን ለመምረጥም አዋጅ። ንጉሡም በአገልጋዮች አማካይነት ንግሥት የምትሆነው እንድትመረጥ አደረገ። ብዙዎችም በንግሥትነት ለመመረጥ ቀረቡ። ከእነዚህ አንዶም **'አስቴር'** ነበረች።
- በጣም ቋንጆ የነበረችው አስቴር አባትና እናት አልነበራትምና አጎትዋ **'መርዶክዮስ'** አሳደጋት።
- ***መርዶክዮስ*** የንጉሡን አዋጅ ሲሠማ÷ በንጉሡ እንድትመረጥ አቀረባት። ከ12ወራት የውበትና የመንጻት ዝግጅትም በኋላ ቆነጃጅቱ በንጉሡ ፊት ቀረቡ።
- ***አስቴርም በንጉሡና በሚያዩአት ሁሉ ፊት ሞገስ አግኝታ ተመረጠች። የንግሥና ዘውዱንም ደፋች። ንጉሡም ለአስቴር ክብር ታላቅ በዓል አድርጎ ሰዎችን ጋበዘ።***
- ቆንጆዋንና ተወዳጅ የሆነችውን አስቴር ስላገኘም ተደሠተ። ሚስቱ አደረጋት ንግሥት ሆናም ተሾመች።

**ጥያቄዎች**
1. ንጉሡ አስጤክስስ አዲስ ንግሥት ለመሾም ለምን ፈለገ?
2. ተወዳዳሪዎቹ ለንግሥትነት ለመወዳደር ምን ያህል ወር ተዘጋጁ?
3. ንጉሡ ለንግሥትነት ማንን መረጠ?
4. ለአዲሷ ንግሥት መመረጥ ንጉሡ ምን አደረገ?
5. አስቴርን ያሳደገት ማነው? ለምን?
7. ይሄን ታሪክ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እናገኘዋለን?ብሉይ ኪዳን ወይስ አዲስ?

## የቅዱስ ማቴዎስ ለሐዋርያትነት መጠራትና 12 ደቀመዛሙርት፣

**ዓላማ**
- ክርስቶስ ኃጥኣንን ለንስሐ ለመጥራት እንደመጣ መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**
- ***"ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም።"*** ማቴ. 9÷13

**ምንባባት**
- ማቴ. 9÷1-13, ማር. 2 እና 3  ሉቃ. 5 እና 6

**መግቢያ**
- ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት 6ቱን ሐዋርያት እንደጠራ ተምረናል። ስማቸውን ታስታውሳለችሁ?
- ወንድማማቹ እንድሪያስና ጴጥሮስ እንዲሁም ዮሐንስና ያዕቆብ፤ ፊልጶስ ናትናኤልንም ነበሩ።
- የመጀመሪያዎቹ አራት ዓሣ አጥማጆች ነበሩ። ዛሬም የሌሎቹን ሐዋርያት አጠራር እንማራለን።

**ትምህርቱ**
- ከ12 ሐዋርያት አንዱ የሆነው ማቴዎስ ግብር ሰብሳቢ ነበር። ቀራጭ ይባሉም ነበር። ጉቦ የሚቀበሉ ሙሰኞች ስለነበሩ እምነት አጉዳይ ሲባሉ÷ አብዝተው ሕዝቡን ይበዘብዙና ግብር እየጫኑ ለራሳቸው ያተርፉ ነበር።  ከሕዝቡም ጉቦ ይቀበሉ ነበር። ሕዝቡ እንደኃጢአተኛ ያያቸውና ይጠላቸውም ነበር።
- ማቴዎስም ግብር ሰብሳቢ /ቀራጭ/ ነበርና ግብር ለመሰብሰብ በተቀመጠበት ጌታ ሲያልፍ አይቶት። ***"ተከተለኝ"*** አለው። ማቴዎስም ተነስቶ ተከተለው። በዚያው ቀንም ቀራጭና ኃጢአተኞችን ሰብስቦ ጌታችንን በቤቱ እራት ጋበዘው።
- አይሁድ ይሄን አይተው ደቀመዛሙርቱን *'መምህራችሁ ለምን ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል'* አሉት
- ጌታም ***"ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ ነገር ግን ሄዳችሁ፦ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ተማሩ፤ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና አላቸው።"***
- ከዚያ ጀምሮም ማቴዎስ ቀራጭነቱንና ኃጢአቱን ትቶ ተከተለው። የጌታ ደቀመዝሙር/ ሐዋርያም ተባለ።
- ከጌታ እርገት በኋላም ስለጌታችን ልደት ፣ጥምቀት፤ ተዓምራትና የምድር ሕይወት በወንጌል ጻፈልን።
- እያስተማረ ኖሮም በሰማዕትነት አረፈ።
- ጌታችን 12 ደቀመዛሙርት ሲመርጥ ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው እነርሱም ከላይ የተጠቀሱት 6ቱና ማቴዎስ፣የታዲዎስ ወንድም ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣ ስምዖን፣ ቶማስና የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው። በኋላም ይሁዳ ጌታን ስለከዳው በማቲያስ ተተክቶል።

**ይቆየን፡፡**